ፍሬውን እንድናይ ተጠናክሮ ይቀጥል

ብ. ነጋሽ

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና መንግስት ህዝቡን ያስቆጣውንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ለአደጋ ያጋለጠውን ውስጣዊ ችግር ለመፍታት ዳግም በጥልቀት ለመታደስ መወሰናቸውን ካሳወቁን መንፈቅ ሊሞላ ነው። መንግስት ይህን በጥልቀት የመታደስ ውሳኔ ተግባራዊነት የመንግስት አደረጃጀት ለውጥ ከማድረግ እንደሚጀምርም ነግሮን ነበር። የመዋቅር አደረጃጀት ለውጥ ማድረግ ያስፈለገበት ቀዳሚው ምክንያት ደግሞ ለመልካም አስተዳደር መጓደል አንዱ መንስኤ የሆነውን የብቃት ማነስ ለማቃለል ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ስልጣናቸውን ህዝብን ከማገልገል ይልቅ የግል ኑሮ መሰረት ያደረጉ ከዚህም አልፈው የግል ጥቅም ማስጠበቂያ ያደረጉትን የስራ ሃላፊዎች በማስወገድ የህዝብ አገልጋይነት መንፈስና ቁርጠኝነት ያላቸውን አመራሮች ወደስራ ለማምጣት ነው። በዚህ መሰረት በፌዴራልና በክልል መንግስታት የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደዋል።

በተለይ፤ የፌዴራልና የክልል መንግስታት የ5ኛውን ዙር የስልጣን ዘመን 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን መጀመራቸውን ተከተሎ የካቢኔ ሹም ሽር አድርገዋል። በፌዴራል መንግስት በሚኒስትርና አቻ የሃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ አመራሮች ሹም ሽር ተደርጓል። ክልላዊ መንግስታትም ችግር አለባቸው ያሏቸውን የቢሮ ሃላፊዎች በማንሳት በአዳዲስ ተክተዋል። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ደግሞ ከቢሮ ሃላፊዎች ባሻገር የክልሉን ርእሰ መስተዳደርና ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች አንስቶ በአዲስ ተክቷል። በአሁኑ ጊዜ የኢህአዴግ ድርጅቶች የሚመሯቸው አራቱም ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ትግራይ፤ አማራ፤ ኦሮሚያና የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች የካቢኔ ለውጥ አድርገዋል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ተመሳሳይ እርምጃ ወስዷል።

በክልል ደረጃ የመዋቅር ማስተካከያው ወደዞንና የከተማ አስተዳደሮች እየወረደ ነው። የዞን እና የከተማ አስተዳደሮች ሃላፊዎቸ ሲሾሙ ህዝብ ፊት ቀርበው እንዲገመገሙ ይደረጋል። ይህ ከዚህ ቀደም ያለተለመደና የተሃድሶውን ስኬት ያሳልጣል የሚል የህዝብ እምነት የፈጠረ ነው። ህዝብ ያልፈለጋቸው አመራሮች ወደሃላፊነት አይወጡም። ህዝብ ችግር ያለባቸውን ሃላፊዎች ያብጠለጠለውን ያህል በስራቸው ያረኩትን ደግሞ ያሞገሰበት አጋጣሚም ነበር። ይህን በተመለከት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ዱከም ከተማ ከንቲባ የነበሩትን መጥቀስ ይቻላል። ከንቲባው ከዱከም ከንቲባነት ወደሰበታ ከንቲባነት ተዛውረው ሲሾኙ የከተማዋ ነዋሪዎች ከንቲባውን ያስተማራቸውን ዩኒቨርሲቲ ሳይቀር አመስግነው ነበር። ህዝብ እንደዚህ ነው። የሰሩለትን ያሞግሳል፣ ይሸልማል፤ የበደሉትን ደግሞ ይጠላል፣ እድሉን ካገኘም ያጋልጣል።

ይህ የአደረጃጀት መዋቅር ማስተካከያ እርምጃ በጥልቀት የመታደስ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። በጥልቀት የመታደሱ መድረሻ ኪራይ ሰብሳቢነትን በማኮሰስ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ በኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ምክንያት የተበላሸውን የመልካም አስተዳደር ችግር ማቃለል፤ ህዝብ በጉጉት የሚጠብቃቸውን መሰረታዊ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮጀክቶቸ በአግባቡና በወቅቱ አጠናቅቆ ወደአገልግሎት ማስገባት፤ አሁን ያለውን የትላልቅ ፕሮጀክት መጀመር እንጂ፤ መጠናቀቅ በጥርጣሬ እንዲታይ ያደረገውን ሁኔታ በመቀየር የአገሪቱ ኢኮኖሚ እመርታዊ ለውጥና መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያመጣ ማድረግ የሚያስችሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በአግባቡ እንዲጠናቀቁ ማድረግ፤ ፍርድ ቤቶች ህግና ፍትህ የሚከበርባቸው ተቋማት እንዲሆኑ ማድረግ፣ . . . ናቸው።

ህዝብ ይህ እውን ሆኖ የሚያይበትን ጊዜ በጉጉት እየናፈቀ ይገኛል። ህዝብ የተሃድሶውን ውጤት በጉጉት የሚጠባበቀው እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን መድረሻዎች ያመጣል ብሎ ስላመነ ብቻ ነው። ተሃድሶው በእነዚህ መድረሻዎቹ እስካልተገለጸ ድረስ ተሃድሶ ተካሂዷል ወይም እየተካሄደ ነው መባሉ ህዝብን እንደማያረካ፤ ቅሬታውንና ተቃውሞውን ከማሰማት እንደማይገታው መታወቅ አለበት። ለህዝብ መታደስ ማለት ከመንግስት የሚጠበቃቸውን ነገሮች በትክክልና የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው ልክ ማግኘት ማለት ብቻ ነው። ሰሞኑን ተሃድሶው ወደህዝብ ሲወርድ የሰማነውም ይህንኑ ነው።

በጥልቀት የመታደሱ እርምጃ በአደረጃጃት አወቃቀር ለውጥ ብቃት የሌላቸውንና በስልጣናቸው ህዝብን ከማገልገል ይልቅ የኑሮ መደላድል ያደረጉትና አንስቶ በሌላ በመተካት ብቻ የሚገለጽ አይደለም። በተለይ ስልጣናቸውን ለግል መጠቀሚያነት ያዋሉና የማይገባቸውን ጥቅም ያጋበሱና ሌሎች እንዲያጋብሱ ያደረጉ አመራሮች፤ እንዲሁም በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥና ከዚህ ውጭ ያሉ የጥቅም አባሪዎቻቸው በወንጀል እንዲጠየቁም ይጠብቃል። ህዝብ በተለይ፤ ገዢው ፓርቲና መንግስት ስልጣናቸውን ለግል መጠቀሚያነት ያዋሉ አመራሮች መኖራቸውን በይፋ መናገሩን ተከትሎ በወንጀል እንዲጠየቁ ያለውን ፍላጎት በተለያየ አጋጣሚ ሲገልጽ ቆይቷል።

ሰሞኑን የወንጀል ተጠርጣሪዎችን በህግ እንዲጠየቁ የማድረግ በጥልቀት የመታደሱ ሁለተኛው እርምጃ እየተወሰደ ነው። በተለይ የአዲስ አበባ አስተዳደርና የፌዴራል መንግስት የተሰጣቸውን ሃላፊነት ለግል ጥቅም ያዋሉ አመራሮችንና ባለሞያዎችን በሙስና ወንጀል ጠርጥረው ክስ መመስረታቸውን አሳውቀዋል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ 125 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው መሆኑን ሰሞኑን አስታውቋል። በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወኑ የሚገኙ የልማት እንቅስቃሴዎች በሚፈለገው ፍጥነትና የህዝብ እርካታን ሊያመጣ በሚችል አቅጣጫ እንዳይጓዙ እቅንቀፋት ከሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መካከል ቀዳሚው በተለያዩ የመንግስትና የአስተዳደር

ተቋማት ውስጥ በሚገኙ የመንግስት ሃላፊዎች የሚፈፀም የሙስና ወንጀል መሆኑን የከተማዋ ፖሊስ ኮሚሽን በሰጠው መግለጫ አስታውቋል። ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተጀመረውን ሰፊ የጥልቅ ተሃድሶ ንቅናቄ መነሻ በማድረግ ባካሄደው ዘመቻ በተለያዩ የከተማው አስተዳደር መስሪያ ቤቶች ውስጥ በተፈፀመ የሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ 125 ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር አውሎ ምርመራ እያደረገ መሆኑንም አስታውቋል። በፖሊስ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ከዋሉት መካከልም 22 አመራሮች፤ 99 ሰራተኞችና አራት ደግሞ ከመንግስት መዋቅር ውጭ ያሉ ግለሰቦች መሆናቸውን ኮሚሽኑ በመግለጫው አመልክቷል።

ህዝብ በተለይ አመራር የተባሉት 22ቱ የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪዎች ማንነት እንዲነገረው ይፈልጋል። እስካሁን ይህ አለመደረጉ ቅሬታ ፈጥሯል። በዚህ አጋጣሚ፤ ህዝቡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን ማንኛውንም መረጃ የማግኘት መብት እንዳለውም መታወስ አለበት። ግልጽነት አንዱ የመልካም አስተዳደር መገለጫ መሆኑም እንዲሁ!

የከተማዋ ፖሊስ ኮሚሽን እንዳስታወቀው፤ ግለሰቦቹ ከተጠረጠሩባቸው ወንጀሎች መካከል፤ የመንግስት ቤቶች ወደ ግለሰቦች ይዞታነት እንዲዞሩ ማድረግ፤ የተሽከርካሪ ሰሌዳ በህገወጥ መንገድ መስጠት፤ በሌሉ ሰዎች ስም መንጃ ፈቃድ መስጠት፤ የመንግስት ገንዘብ ማጉደል፤ ከህግና ከአሰራር ስርዓት ውጪ ለግለሰቦች ያለጨረታ ስራዎችን መስጠት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በተመሳሳይ፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንም በፌደራል መንግስት ተቋማት ውስጥ በሙስና ወንጀል ጠርጥሬያቸዋለሁ ያላቸውን ግለሰቦች በቁጥጥር ስር አውሎ ምርመራ እያካሄደ መሆኑን አሳውቋል። በዚህም 130 ግለሰቦች በሙስና ወንጀል ጠርጥሮ በቁጥጥር ስር ማዋሉን ነው የነገረን፤ መንግስት የጀመረው በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ላይ በመመስረት ከህዝብ፤ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች 260 ጥቆማዎች እንደደረሱትና በነዚህ ጥቆማዎች መነሻነት ባደረገው ማጣራት ከ130 በላይ ተጠርጣሪዎችን በከባድ የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪ ሆነው መገኘታቸውን አስታውቋል።

ተጠርጣሪዎቹ የመንግስት አመራሮች፤ ባለሙያዎችና የተለያዩ ግለሰቦች መሆናቸውም ተነግሮናል። ልክ እንደአዲስ አበባው ሁሉ፤ የመንግስት አመራሮቹ ማንነት በኮሚሽኑ አለመገለጹ ህዝቡን ቅር ያሰኘው መሆኑ መታወስ አለበት። ከሙስና ወንጀል ተጠረጣሪዎቹ ጋር ተያይዞ 13 የሃብት እና የንብረት እገዳ ማድረጉን ያሳወቀው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፤ እነዚህም 8 ትላልቅ የአክሲዮን ኩባንያዎች፤ 2 ፋብሪካዎች፤ 4 ህንፃዎች፤ 22 መኖሪያ ቤቶች እና 49 ተሽከርካሪዎች እንደሆኑ አስታውቋል።

በፌደራል ፖሊስ መግለጫ ላይ የተጠቀሰው በተጠርጣሪ ሙሰኞች ላይ የደረሰው የህዝብ ጥቆማ መንግስት በይፋ ባወጀው በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ውስጥ ህዝብ እየተሳተፈ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ በተጓዳኝ፤ በየአካባቢው ከመንግስት አፈጻጸም ጋር በተገናኘ ከህዝብ ጋር የሚካሄዱ ውይይቶችና ህዝብ በሚሾሙለት አመራሮች ላይ አስተያየት እንዲሰጥ የማድረግ አካሄድም በጥልቀት የመታደሱ እንቅስቃሴ ወደህዝቡ እየወረደ መሆኑን ያመለክታል።

በአጠቃላይ፤ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና መንግስት በይፋ የጀመሩት በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ወደፊት እየተራመደ መሆኑንና በተለይ ወደህዝብ መውረዱ የሚሳካ መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም፤ ህዝብ ከሂደቱ ይልቅ ውጤቱ ላይ አተኩሮ እየተከታተለ በመሆኑ የበለጠ ፍሬውን ለማየት ተሃድሶው ተጠናክሮ ይቀጥል።